ጥር 2003

ጥቅል ሀገራዊ ዘገባ

# ኢትዮጵያ

ገዢው የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር(ኢሕአዲግ) በግንቦት ወር 2002 የተደረገውን የፓርላማ ምርጫ 99.6 በመቶ በሆነ አስደናቂ ውጤት በማሸነፍ የፖለቲካ ቁጥጥሩን አጠናክሮአል። የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ ሰላማዊ የነበረ ቢሆንም ከምርጫው በፊት በነበሩት ወራት የተቃዋሚ ፓርቲዎች ደጋፊዎችን ማሳደድና ለገዢው ፓርቲ ድጋፍ ማሰባበሰብን ዓላማ ያደረገ ሰፊ ዘመቻ በመንግስት ተካሂዷል። ይህም በመንግስት የሚሰጡ አገልግሎቶችና ድጋፎችን ለገዢው ፓርቲ ደጋፊዎች ብቻ እንዲሰጡ ማድረግን የሚጨምር ነበር።

ምንም እንኳን መንግስት ታዋቂዋን የፖለቲካ እስረኛ ከሁለት ዓመት እስር በኋላ በጥቅምት 2003 ከእስር የፈታ ቢሆንም በመቶዎች የሚቆጠሩ ሌሎች የፖለቲካ እስረኞች የሰቆቃና የመንገላታት አደጋ ውስጥ ሆነው በእስር ላይ ይገኛሉ። የግንቦቱን ምርጫ ተከትሎ የፖለቲካ አፈናው ጋብ ይላል የሚል ተስፋ የነበረ ቢሆንም በዓመቱ መጨረሻ መንግስት በነፃ የሲቪል ማህበረሰቡ እና በመገናኛ ብዙሃን ላይ የሚያደርገው ጥቃት አልቀነሰም።

### የግንቦት 2002 ምርጫ

ገዢው ፓርቲ የ2002ን ምርጫ ያሸነፈበት እጅግ ሰፊ የሆነ ውጤት ለብዙ ታዛቢዎች አስገራሚ የነበረ ቢሆንም ገዢው ፓርቲ ምርጫውን እንደሚያሸንፍ አስቀድሞ የተገመተ ነበር። የምርጫው ውጤትም በሀገሪቱ በ 2000 ዓ.ም ተካሂዶ የነበረውን የአካባቢ ምርጫ ውጤት የደገመ ነው። የ99.6 በመቶው ውጤት መንግስት ለአምስት ዓመታት ሲከተለው የቆየው ለፖለቲካ ተቃውሞና ነፃ አስተያት ያለውን ምህዳር በስልት የመዝጋት ስትራተጂ የደረሰበትን ከፍተኛ ደረጃ ያሳየ ነው። የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢዎች ቡድን ምርጫው ዓለማቀፍ የምርጫ መመዘኛዎችን ያሟላ አልነበረም ብሏል።

በ2002ቱ ምርጫ መዳረሻ ጊዜያት በትግራይ ክልል የተቃዋሚ ዕጩ የነበረውን የአረጋዊ ገብረዮሃንስን ግድያ ጨምሮ አንዳንድ የሀይል ጥቃቶች ተስተውለዋል። ብዙ ጊዜ መራጮች ማስፈራራት፣ዛቻና ማስገደድ ይደርስባቸው ነበር። እስከ መንደር ደረጃ የተንሰራፋው የኢትዮጵያ መንግስት የስለላ ሥርዓት በአብዛኛው በገጠር ነዋሪ በሆነውና ሰማኒያ ሚሊዮን በሚሆነው የሀገሪቱ ሕዝብ ላይ በቀበሌና በንዑስ ቀበሌ የአስተዳደር መዋቅሮች አማካይነት ጫናውን ያሳርፋል።

መራጮች ገዢውን ፓርቲ እንዲቀላቀሉ ወይም ድጋፍ እንዲሰጡ የእህል ዘር፣ የማዳበሪያ፣ የእርሻ መሳሪያዎች እና ብድርን የመሳሰሉ ማባበያዎችና የሚቀርቡላቸው ሲሆን ተቃዋሚ ፓርቲዎችን የሚደግፉ ከሆነ ደግሞ በመንግስት መስሪያ ቤቶች የሥራ እድል መነፈግን፣ የትምህርት እድሎችን እንዲሁም የምግብ ዕርዳታን መከልከልን የመሳሰሉ አድሎአዊ ቅጣቶች ይፈጸሙባቸዋል። በሚያዚያ እና በግንቦት ወራት የአካባቢ አስተዳደርና ሚሊሻያ አባላት ቤት ለቤት እየዞሩ ነዋሪዎች በመራጭነት እንዲመዘገቡና ድምጻቸውን ለገዢው ፓርቲ እንዲሰጡ ይህ ካልሆነ ግን በአስተዳደር ውጣ ውረድ መንገላታትን ጨምሮ ሥራቸውንና ቤቶቻቸውን ማጣትን የመሳሰሉ የቅጣት እርምጃዎች ሊፈጸሙባቸው እንደሚችሉ ይነግሩ ነበር።

**የፖለቲካ አፈና፣ ከፍርድ በፊት እስርና ማሰቃየት**

እ.ኤ.አ በ 2010 በኢትዮጵያ ከታዩት ጥቂት አወንታዊ የፖለቲካ እርምጃዎች መካከል አንዱ መንግሰት የተቃዋሚው የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ መሪ የሆነችውን ብርቱካን ሚደቅሳ ከ ሃያ ሁለት ወራት እስር በጥቅምት ወር መፍታቱ ነው። ብርቱካን ከሌሎች የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ጋር በ 1997 ዓ.ም ታስራ የነበረ ሲሆን ሁለት ዓመት ከሚጠጋ እስር በኋላ በ 1999 በይቅርታ ከእስር ተለቃ ነበር። ከዚያም በታህሳስ 2001 እንደገና ለእስር ተዳርጋለች። እ.ኤ.አ በ2009 የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ኤክስፐርቶች የብርቱካን እስር የዘፈቀደና ዓለምአቀፍ ሕግን የጣሰ መሆኑን አረጋግጠዋል።

በመቶዎች የሚቆጠሩ ሌሎች ኢትዮጵያውያን በሕገ ወጥ ሁኔታ ታስረው አንዳንድ ጊዜም ሰቆቃና ማንገላታት እየተፈጸመባቸው በቁጥጥር ስር ይገኛሉ። በቁጥጥር ስር  የሚገኙ ሰዎች የሚገኙባቸውን ቦታዎች ለመጎብኘት የተፈቀደለት አንድም የሀገር ውስጥም ሆነ ዓለማቀፍ ድርጅት የለም። በመሆኑም በሀገሪቱ እስር ቤቶች የሚገኙ የፖለቲካ እስረኞችንና ሌሎች ያላግባብ ታስረው የሚገኙ ሰዎችን ቁጥር በትክክል ለማወቅ አልተቻለም።

የኢትዮጵያ መንግስት የፖሊስ፣ የመከላከያ ሰራዊትና ሌሎች የጸጥታ ሀይሎች አባላት የመንግሰት ተቃዋሚ ናቸው ተብለው የሚታሰቡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን፣ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አባላትን፣ የታጠቁ አማጽያን ደጋፊዎች ናቸው የተባሉ ግለሰቦችንና በሽብርተኝነት የተጠረጠሩ ሰዎችን ለመቅጣት ማሰቃየትንና ማንገላታትን ይፈጽማሉ። ምስጢራዊ የእስር ቦታዎችና ወታደራዊ ካምፖች ብዙ ጊዜ ለዚህ ዓይነቱ ድርጊት በኢትዮጵያ የጸጥታ ሃይሎች ጥቅም ላይ ይውላሉ። ምንም እንኳን ለመሠረታዊ ሰብአዊ መብቶች ጥበቃ የሚያደርጉ ድንጋጌዎች በኢትዮጵያ የወንጀልና ሌሎች ሕጎች የተካተቱ ቢሆንም እነዚህ ድንጋጌዎች በአብዛኛው ጊዜ ተፈጻሚ አይሆኑም። በፍጥነት ምርመራ የሚደረግባቸው የማሰቃየት ድርጊቶች እጅግ በጣም ጥቂት ሲሆኑ ለፍርድ የሚቀርቡት ደግሞ ከዚህም ያነሱ ናቸው።

በትጥቅ ትግል ከተሰማሩት እንደ ኦሮሞ ነጻነት ግንባር እና በሶማሌ ክልል ከሚንቀሳቀሰው የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር ከመሳሰሉት ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው በተጠረጠሩ ሰዎች ላይ የሚፈጸመው የማሰቃየትና የማንገላታት ድርጊት እጅግ አሳሳቢ ነው። የኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት እና ሌሎች የጸጥታ ሃይሎች የጦር ወንጀሎችን ጨምሮ ሌሎች ከባድ ወንጀሎችን በሶማሌ ክልል ፈጽመዋል። ይሁንና ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ የኢትዮጵያ መንግስት እነዚህን ወንጀሎች ለመመርመርም ሆነ ፈጻሚዎቹን ለፍርድ ለማቅረብ አንድም ተአማኒነት ያለው ጥረት አላደረገም።

**ሐሳብን የመግለጽ ነጻነትና የመደራጀት መብት**

እ.ኤ.አ በ 2009 መጨረሻና በ 2010 መንግስት ነጻ አስተሳሰብ በሚያራምዱ ወገኖችና ድርጅቶች ላይ የሚያደርገውን ዘመቻ አጠናክሮ ቀጥሎአል። ከዚህም በላይ ኢትዮጵያውያን መረጃ የሚያገኙበትን መንገድ ገድቧል። የፓርላማ ምርጫ ከተካሄደበት ከግንቦት 2002 በፊት ብዙዎቹ ዋነኛ ነጻ ጋዜጠኞችና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች በደረሰባቸው ግልጽና ስውር ዛቻዎች ምክንያት ሀገሪቱን ጥለው ለመሄድ ተገደዋል። ጥቂት ነጻ ጋዜጦች መታተማቸውን የቀጠሉ ቢሆንም ራሳቸውን ሳንሱር የሚያደርጉ ናቸው።

በስርጭት ብዛት ቀዳሚ የነበረውን አዲስ ነገር የተባለውን ጋዜጣ ለመክሰስ በ 2001 ዓ.ም የወጣውን የፀረ ሽብርተኝነት ሕግ በመጥቀስ ከመንግስት በደረሰባቸው ማስፈራራት የጋዜጣው አዘጋጆች ጋዜጣውን በመዝጋት ሀገሪቱን ለመልቀቅ ተገደዋል። ይህ ከሆነ ከጥቂት ቀናት በኋላ ጋዜጣውን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ለማስፈጸም ይከታተል የነበረው የአዲስ ነገር አስተዳዳሪ በፖሊስ ተደብድቦአል።

ሌሎች ጋዜጦችም ዛቻ ወይም ጥቃት ደርሶባቸዋል።የጋዜጠኞች መብት ጥበቃ ድርጅት እ.ኤ.አ ከ 2009 መጨረሻ እስከ ግንቦት 2010 ባለው ጊዜ ብቻ 15 ጋዜጠኞች ሀገሪቱን ለቀው መሄዳቸውን ዘግቧል። ለመገናኛ ብዙሃን ሥራ ፈቃድ የሚሰጠው የመንግስት መስሪያ ቤት አንድ ባለስልጣን አውራምባ ታይምስ የተባለው ጋዜጣ "ሕዝብን ለአመጽ ለማነሳሳት እና ለማደናገር ሆን ብሎ ይንቀሳቀሳል።" በማለት ተናግረዋል። በነሃሴ ወር የጋዜጣው ቢሮ መስኮቶችና በሮች ባልታወቁ ሰዎች ተሰባብረዋል። በመስከረም ወር ሰንደቅ የተባለው ጋዜጣ ከአንድ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪ ጋር ያደረገውን ቃለ ምልልስ አትሞ ካወጣ በኋላ የጋዜጣውን አዘጋጅ ፖሊስ ለምርመራ ጠርቷል። የምርመራው ምክንያትም ጋዜጣው የሥራ ፈቃድ ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ነው ተብሏል።

በመጋቢት ወር የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በ 1997 ዓ.ም የተካሄደውን የፓርላማ ምርጫ በመዘገባቸው ብቻ በ1999 ሕገ መንግስቱን በሃይል ለመናድ በሚል ወንጀል ተከሰው የተፈረደባቸው አራት የአሳታሚ ድርጅቶች ባላቤቶች ላይ ተጥሎ የነበረውን ከባድ የገንዘብ ቅጣት መልሶ ተፈጻሚ እንዲሆን ትዕዛዝ ሰጥቶአል። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያን የኦርቶዶክስ ክርስቲያን ሃገር እንደሆነች አድርገው በማቅረብ መናገራቸውን ከሁለት ዓመት በፊት በጻፈው ጽሁፍ የተቸው አል ቁድስ የተባላው ጋዜጣ አዘጋጅ በየካቲት ወር በአንድ ዓመት እስራት እንዲቀጣ ፍርድ ቤት ወስኖበታል።

ለውጭ መገናኛ ብዙሃንም ቢሆን ሁኔታው ከዚህ ብዙም የተሻለ አይደለም። መንግስት የአሜሪካ ድምፅ ሬድዮ በአማርኛ፣በኦሮምኛ እና በትግርኛ ቋንቋዎች የሚያስተላልፋቸውን ፕሮግራሞች እንዳይሰሙ በየካቲት ወር ያፈነ ሲሆን በመቀጠልም የጀርመን ድምጽ ሬድዮ ፕሮግራሞችን አፍኖአል። ይህ የሬድዮ ጣቢያዎችን የማፈን ድርጊት በነሀሴ ወር አብቅቶአል። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የሬድዮ ጣቢያዎቹ ሩዋንዳ ውስጥ የዘር ማጥፋትን አጀንዳ ያቀነቅን ከነበረው የሬድዮ ጣቢያ ጋር በሚመሳሰል "አለመረጋጋትን የሚያስፋፋ ፕሮፓጋንዳ በማሰራጨት ላይ የተሰማሩ ናቸው" በማለት ስርጭቶች የማፈኑን ተግባር ትክክለኛነት በመደገፍ ተናግረዋል።

በነጻ ተቋማት ላይ የሚደርሰው ጥቃት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በተለይም በሰብአዊ መብቶች ሥራ ላይ የተሰማሩትን የሚነካ ነው። በ2001 ዓ.ም የወጣው አፋኙ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ከአስር በመቶ በላይ ገቢያቸውን ከውጭ ምንጮች የሚያገኙ ኢትዮጵያውያን መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሰብአዊ መብቶችና በመልካም አስተዳደር ሥራዎች ላይ እንዳይሰማሩ ይከለክላል።

የዚህ ሕግ መውጣት በዝግታ በማደግ ላይ በነበረው የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ላይ ያስከተለው ውጤት እንደተገመተው እጅግ አውዳሚ ነበር። ዋነኞቹ የሰብአዊ መብቶች ድርጅቶች በሕጉ መውጣት ሳቢያ የተሽመደመዱ ሲሆን ብዙዎቹ የድርጅቶቹ መሪዎች መንግስት ለነፃ የሰብአዊ መብቶች ተሟጋቾች በሚያሳው አንዳንድ ጊዜ በጣም ግልጽ የሆነ የጠላትነት ስሜት ምክንያት ሀገር ጥለው ተሰደዋል።

እ.ኤ.አ በ2009 መጨረሻ ሁሉም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አዲስ በተቋቋመው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ እንደገና እንዲመዘገቡ ግዴታ የተጣለባቸው ሲሆን በዚህ ሂደት አንዳንዶቹ ድርጅቶች ሰብአዊ

መብቶችን የሚመለከቱ ሥራዎችን ከሥራ ዝርዝሮቻቸው ውስጥ አስወግደዋል። የሰብአዊ መብቶች ክትትል ሥራ ላይ እንደተሰማራው አንጋፋው የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) እና የቤት ውስጥ ጥቃትና የሴቶች መብቶችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ጠቃሚ ሥራዎችን እንደሚያከናውነው የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር ያሉ ሌሎች ድርጅቶች በጀታቸውን፣ የሠራተኞቻቸውን ቁጥርና የሚያከናውኗቸውን ሥራዎች በከፍተኛ መጠን ቀንሰዋል። መንግስት የሁለቱን ድርጅቶች የባንክ ሒሳቦች እንዳይንቀሳቀሱ እ.ኤ.አ በታህሳስ 2009 በማገድ ድርጅቶቹ መጠቀም የሚችሉት የታገደውን ገንዘብ 10 በመቶ ብቻ እንዲሆን ፈቅዷል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ መንግስት የገዢው ፓርቲ አጋር የሆኑ ድርጅቶችን የተፈጠረውን ክፍተት እንዲሞሉ እያበረታታ ሲሆን ከእነዚህም አንዱ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ይገኝበታል።ይህ ኮሚሽን አንዳችም ዓይነት ነፃነት የሌለው ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም ነው።

**ቁልፍ ዓለማቀፍ ተዋናዮች**

አካባቢያዊ የጸጥታ ስጋቶች በተለይም ደግሞ መጪው የሱዳን ውሳኔ ሕዝብ እና እያደገ የመጣው የሶማሊያ እስላማዊ ታጣቂ ቡድኖች መስፋፋት የምዕራብ ሀገራት ለጋሾች በኢትዮጵያ ላይ ሰብአዊ መብቶችን አስመልክቶ ግፊት እንዳያደርጉ እስካሁን ድረስ ገድቧቸው ይገኛል። እየከፋ የሄደውን የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ በሚመለከት የኢትዮጵያ አፍሪካዊ ጎረቤቶች ዝምታን የመረጡ ሲሆን፤ የሚያደርጉት አስተዋጽኦ በምእራብ ሀገራት ከሚሰጠው ዕርዳታ ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ ቢሆንም ቻይና፣ደቡብ ኮርያ እና ጃፓንም እ.ኤ.አ በ 2010 ከኢትዮጵያ ጋር የሚያደርጉትን ትብብር ጨምረዋል። ከቻይና የሚገኘው ገንዘብ በአብዛኛው ለመሠረተ ልማቶች ግንባታ የሚውል ቢሆንም እንደ ዘ ኢኮኖሚስት ዘገባ የንግድ ግንኙነቱም በ 27 በመቶ በማደግ ኢ.ኤ.አ በ 2010 የመጀመርያ ስድስት ወራት ብቻ ከ 800 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ ሆኗል።

በግንቦት 2002 ዓ.ም ከተካሄደው ምርጫ በፊትና በኋላ በነበሩት ወራት እየከፋ በመጣውና ሀገሪቱን ሰቅዞ በያዛት የፖለቲካ አፈና ላይ አስተያታቸውን በይፋ የሚሰጡ ሀገራት ቁጥር እጅግ በጣም ጥቂት ነው። በግንቦት ወር 2002 እጅግ ባልተለመደ ሁኔታ ዩናይትድ ስቴትስ “ምርጫውን ነፃና ፍትሐዊ መንገድ ለማካሄድ የሚያስችል አመቺ ከባቢ ከድምጽ መስጫው ቀን በፊትም ቢሆን አልነበረም” በማለት ሀሳቧን ገልጻለች። የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢዎች ቡድንም ለሁሉም ወገኖች እኩል የተመቻቸ የመጫወቻ ሜዳ ካለመኖሩና በመደራጀትና ሐሳብን በነጻ በመግለጽ መብቶች ላይ ከተጣሉት ገደቦች ጋር የተያያዙ በርካታ ችግሮችን አውስቶአል። ይሁንና የምርጫው ውጤት ኢሕአዴግ የአንድ ፓርቲ መንግስትነቱን ያጠናከረበት መሆኑን የሚያረጋግጥ ሆኖ እያለ ለጋሽ ሀገራት በመንግስት በኩል የሚሰጡትን እጅግ ከፍተኛ መጠን ያለው የልማት ዕርዳታ ቀጥለዋል። እ.ኤ.አ በ 2008 ብቻ የኢትዮጵያ መንግስት ከሦስት ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ የልማት ዕርዳታ ተቀብሏል።

የኢትዮጵያን የሰብአዊ መብቶች አያያዝ የገመገመው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት ዩኒቨርሳል ፒሪዮዲክ ሪቪው የመጨረሻ ሪፖርት እ.ኤ.አ በመጋቢት ወር 2010 ጸድቆ ወጥቶአል። ኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኛ ሰዎች መብቶች ስምምነትን ለማጽደቅ ተስማምታለች። የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን ሕግ እንድትሽር ወይም እንድታሻሽል እንዲሁም የሀገሪቱ የጸጥታ ሃይሎች ለሚፈጽሙት የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ያለውን በሕግ ያለመጠየቅ ሁኔታ እንድታስቆም የቀረበላትን ሃሳብ ውድቅ አድርጋለች።